# ት ም ህ ር ት
# ዘኦርቶዶክስ ተዋህዶ

## ደብረ ታቦር ማቴ ፲፯፥፩-፲፬

ደብረ ታቦር ማለት የታቦር ተራራ ማለት ነው። የሚገኘው ከገሊላ ባሕር በምሥራቃዊ ደቡብ በኩል አስር ኪሎ ሜትር ራቅ ብሎ ነው። የታቦር ተራራ በሐዲስ ኪዳን በግልጽ ባይጠቀስም በብሉይ ኪዳን ግን ተጠቅሶ እናገኛለን (መሳ ፬፤፮-፲፬)።

የተወደዳችሁ ክርስቲያኖች፥ ጌታችን «ሰዎች የሰውን ልጅ ማን ይሉታል?» ብሎ ከስድስት ቀን በፊት በፊልጶስ ቂሣርያ ደቀ መዛሙርቱን በጠየቃቸው ጊዜ አንዳንዱ መጥምቁ ዮሐንስ፣ ሌሎችም ኤልያስ፣ ሌሎችም ኤርምያስ ወይም ከነቢያት አንዱ ነው ይላሉ ብለውት ነበር። እናንተስ ማን ትሉኛላችሁ ሲላቸው ቅዱስ ጴጥሮስ «አንተ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ» ብሎ መልሶለት ነበር። እግዚአብሔር አብ ለቅዱስ ጴጥሮስ ስለ ክርስቶስ ከገለጸለት ከስድስት ቀን በኋላ ሐዋርያት ሰዎች ኤልያስ፣ ኤርምያስ፣ ከነቢያት አንዱ ነው ይሉሃል ካሉት ከስድስት ቀን በኋላ፤ እሞታለሁ፣ እሰቀላለሁ ሲል ቅዱስ ጴጥሮስ ልትሞት አይገባህም ሲለው በጴጥሮስ አንጻር ሰይጣንን ከኋላዬ ወግድ ካለው ከስድስት ቀን በኋላ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሐዋርያት ሦስቱን ይዞ ወደ ተራራ ወጣ።

ወደ ተራራው ከወጣ በኋላ በፊታቸው ተለወጠ፤ ሐዋርያቱ የክርስቶስን የክብሩን ብርሃን ሲያዩ ፊቱ ሲለወጥባቸው በሐዋርያት ልብ ያደረው ሥጋዊ መንፈስ ራቀ፤ በውስጣቸው ያለው ጨለማ ተወገደ። የእግዚአብሄርን ክብር እንዲያስተውሉ አእምሮአቸው ብሩህ ሆነ።

በቤተ ልሔም የተወለደው፣ በበረት- ጽዳት በጐደለው ቦታ የተኛው፣ በአሮጌ ጨርቅ የተጠቀለለው፣ ከብቶች ያሟሟቁት፣ መዋቲ ደካማ ሥጋ የለበሰው ደሃ መስሎ በአርአያ ግብር የታየው ጌታ ክብሩ በዚያ ተራራ ተገለጠ፤ ፊቱ ተለወጠ። እንደ ጸሐይ አበራ ለሐዋርያት በውስጣቸው ያለውን የጨለማ ፍርሃት ያለማወቅ ነገር ኑፋቄ፣ ጥርጥር፣ ክፉ መንፈስ፣ አለማመን፣ ሥጋዊነት … እነዚህን ነገሮች ሁሉ ከልቡናቸው አስወገደላቸው። በብርሃነ መለኮቱ



እንዲራመዱ አደረጋቸው፣ ክብሩን ገለጠላቸው። እኒያ በብዔል ዜቡል ነው አጋንንትን የሚያወጣው ያሉ አሁን ክብሩን ባዩ!

ጌታችን ሙሴን ከመቃብር፣ ኤልያስን ከብሔረ ሕያዋን ያመጣቸው ሙሴ ክብርህን አሳየኝ ብሎት ነበር (ዘጸ ፴፫፤፲፯-፳፫)፤ ጌታችን ግን በሕይወተ ሥጋ እያለ እኔን ሊያይ የሚቻለው ማንም የለም ብሎት

# ደብረ ታቦር ...

ነበር። ሙሴ ሲሞት ጸሎቱ እንዳልተመለሰለት አድርገን ልናይ እንችላለን፤ የፍጥረትን ጸሎት የማይዘነጋ እግዚአብሔር ግን የሙሴን ጸሎት ሳይረሳ ልመናውን ፈጸመለት።

የተወደዳችሁ ክርስቲያኖች፥ ጌታችን በደብረ ታቦር ተራራ የብሉይ እና የሐዲስ ኪዳን ሰዎችን (ነቢያትን እና ሐዋርያትን) አንድ አደረጋቸው። እርሱ አምላካችን መጋቤ ብሉይ ወሐዲስ፣ ሠራኤ ብሉይ ወሐዲስ ነውና። ሌላው ሙሴና ኤልያስ የተጠሩበት «ሙሴ ነህ ያላሉ፣ ኤልያስ ነህ ይላሉ» ሲሉት እርሱ አምላከ ሙሴ አምላከ ኤልያስ መሆኑን ሊያሳይ ነው።

ቅዱስ ጴጥሮስ ጌታችንን በዚህ ለእኛ መኖር እንዴት መልካም ነው፤ ዳስ እንስራ ብሎት ነበር። ወዲያው ብሩህ ደመና ጋረዳቸው፣ ደመና የእግዚአብሔር ክብር ምሳሌ ነው። እነሆ በደመናው ውስጥ የምወደው የምወልደው ለተዋህዶ ለሰማእትነት የመረጥሁት ልጄ ይህ ነው እርሱን ስሙት የሚል ቃል ተሰማ።

በቀዳማዊ አዳም በደልና ነውር የተዘጋው ደጅ በዳግማዊው አዳም በኢየሱስ ክርስቶስ ተከፈተ። ሞት ለተፈረደበት ቀዳማዊው አዳም ብርሃን የለበሰ ጽድቅን የተጎናጸፈ እንደ ጸሐይ የሚያበራ ንጹሕ ባሕርይ ከአእላፍ የተመረጠ እርሱን ኢየሱስ ክርስቶስን እንድንሰማ የባሕርይ አባቱ ተናገረ።

ክርስቲያኖች ሆይ፥ በደብረ ታቦር የአምላካችንን ክብሩን አየን። ዛሬም ያ ክብሩ ለእኛ ለሁላችን ሊገለጥልን ያስፈልጋል። እግዚአብሔር ክብሩን የገለጠበት ያ ተራራ ዛሬ የእኛ አካል ሊሆን ያስፈልጋል። የእግዚአብሔር ክብርና ጥበቡ የሚገለጥበት፣ ማዳኑ የሚታይበት የተባረከ ሕይወት ሊኖረን ይገባል።
ብርሃነ መለኮቱን ካዩ በኋላ የእነቅዱስ ጴጥሮስ የቃላቸው ትምህርት እና የእጃቸው ተኣምራት ብቻ ሳይሆን የልብሳቸው ቁራጭ እና ጥላቸው ሁሉ ጋኔን ያወጣ ይፈውስ ነበር።

ሐዋርያት ጌትነቱ የታየባቸው ደብረ ታቦር ሆነዋል። ቃሉ በሕይወታቸው ተተርጉሞ ነበርና። ዛሬ የክርስቶስን ክብር የሚገልጸው ግዑዙ ደብረ ታቦር ሳይሆን ቅዱስ ሥጋውን የበሉ ክቡር ደሙን የጠጡ የእርሱ ደብረ ታቦሮች ጌትነቱ የሚታይባቸው፣ ግርማው የሚነበብባቸው፣ ጸጋው የተትረፈረፈላቸው፣ አባቶች ካህናት ወንድሞች ዲያቆናት እንዲሁም መላው ምእመናን ናቸው።

ክርስቲያኖች ሆይ፥ ዛሬስ በእኛ በምእመናን ሕይወት የእግዚአብሔር ክብር ይገለጥ ይሆንን? ማነው የክርስቶስ ክብር በሕይወቱ የተገለጠበት? የዓለም ውበትና ጌጥ ሳይሆን የክርስቶስ ጌትነት በውስጣችን ሊገለጥ ይገባል።

ብርሃነ መለኮቱን የገለጸልን አምላክ ስሙ የተመሰገነ ይሁን።

እግዚአብሔር ክብሩን የገለጠበት ያ ተራራ ዛሬ የእኛ አካል ሊሆን ያስፈልጋል።


EthiOrthodox e-mail Outreach EthiOrthodox@AOL.COM